የወ/መ/ቁጥር 160257

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ ትዕዛዙ ወርቁ መኮንን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ህዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም በተሻሻለ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በአንደኛው ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ መስከረም 25 ቀን 2002 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፥00 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/14 ልዩ ቦታው መንዲዳ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሀም የተባሉትን የግል ተበዳይ ብስብስ፤ ወስፋታም፤ የስንዴ ሌባ ብሎ በቀጥታ በመናገር ክብራቸውን የነካ በመሆኑ በፈፀመው የስድብና ማዋረድ ወንጀል፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 244(2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ከላይ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሀም የተባሉትን ግለሰብ ይዘውት የነበረውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማን የዚህ አይነት ባንዲራ እኛ አናውቅም በማለት ከእጃቸው ላይ ነጥቆ መሬት ላይ በመጣል ያዋረደ በመሆኑ በፈፀመው ያገራቱን ምልክቶች መድፈር ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም በሰጡት ቃል፤ በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ ተከሳሽ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ሸዋነሽ አብርሀም የተባሉትን ብስብስ በማለት በመናገር የስድብና ማዋረድ ድርጊቱን መፈፀሙን፤ እንዲሁም በወቅቱ የባንዲራ ቀን ይከበር ስለነበር የግል ተበዳይ የኢፌዲሪን ባንዲራ ይዛ እያለች ይህን ባንዲራ አናውቀውም በማለት ከግል ተበዳይ እጅ ቀምቶ መሬት ላይ የጣለ መሆኑን አስረድተዋል። በዚህም መሰረት ተከሳሽ በሁለቱም ክሶች ላይ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው የተረጋገጠ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 244(2) እና 615 ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡት በወቅቱ የስድብና ማዋረድ ድርጊቱንም ሆነ ባንዲራ ረግጧል የተባለውን ድርጊት አለመፈፀሜንና በወቅቱም የግል ተበዳይ ባንዲራ እንዳልያዘች አስረዳለሁ የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረትም

የመከላከያ ምስክሮቹ ቀርበው እንደ እምነታቸው መጋላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ስንመረምር አንደኛዋ የመከላከያ ምስክር በወቅቱ የሚሰፋ ልብስ ከተከሳሽ ጋር ስለነበረኝ ለማምጣት ስሄድ፤ የተከሳሽ ባለቤት የከሰል መነገጃውን መደብ እያፈረሱ ደርሰኩና ተከሳሽ ስላልነበሩ እየጠበኩ ነበር፤ በኋላ ግን እንደመጡ የግል ተበዳይ ተከሳሽን መስደብ ጀመረች በማለት መስክራለች። ተከሳሽ በወቅቱ በቦታው ያልነበሩ ሆነው፤ በኋላ ሲመጡ ምንም ነገር ሳይናገሩ የግል ተበዳይ የስድብ ውርጅብኝ ታወርድ ነበር ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ፤ የመከላከያ ምስክሯን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ሁለተኛዋ የመከላከያ ምስክርም የተከሳሽ ባለቤት ስለሆኑ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ተከሳሽ

በጭብጡ ያስመዘገበውን ከመድገም ውጭ እውነተኛውን ነገር ይናገራሉ ብሎ ፍ/ቤቱ እምነት የሚጥልባቸው ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ ይልቅ የግል ተበዳይም ሆነ የተከሳሽ ጎረቤቶች የሆኑት የዐ/ሕግ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት እንደተረጋገጠው ተከሳሽ ድርጊቱን መፈፀማቸውን እንጅ አለመፈፀማቸውን የሚያመለክት ነገር አልተገኘም። በመሆኑም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል ያልቻሉ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 244(2) እና 615 ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ በተከሳሽ ላይ የምናቀርበው የቅጣት ማክበጃ የለም፤ ነገር ግን ተከሳሽ በሁለት ድርጊቶች ጥፋተኛ የተባሉ ስለሆነ ቅጣቱ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 መሰረት ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 61 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ አለኝ፤ የትምህርት ደረጃዬ 6 ኛ ክፍል ነው፤ የምተዳደረው በቀን ስራ ከሰል እየቸረቸርኩ ሲሆን በቀን አምስትም አስርም ብር አገኛለሁ፤ ሀገሬን በውትድርና 7 ዓመት አገልግዬ የቀኝ እግሬ ተጎድቶ አሁን በአርቲፊሻል እግር ነው የምኖረው፤ ባለቤቴም ሆነ እኔ የኤች አይ ቪ በሽተኞች ነን፤ ሁለት አካለመጠን ያላደረሱ የ 6 እና 11 ዓመት ልጆች አሉኝ፤ ባለቤቴ ስራ የላትም በማለት አመለከቱ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለችበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615/የስድብና ማዋረድ ወንጀል እና የወንጀል ሕግ አንቀፅ 244(2) በመንግስት የታወቁ ምልክቶችን መድፈር ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የስድብና ማዋረድ ወንጀል አፈፃፀሙ ሲታይ ተከሳሽ የተለየ ድርጊታቸውን ከባድ የሚያደርገው ነገር ፍ/ቤቱ ስላላገኘ፤ እንዲሁም ሁለተኛው የወንጀል ድርጊትም ከራሱ ከአፈፃፀሙ ውጭ የሚያከብድ ነገር ስለሌለው ደረጃዎቹ ዝቅተኛ ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 615 ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት፤ ለወንጀል ሕግ አንቀፅ 244 ላይ ለተመለከተው ደግሞ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ያስቀጣል። ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች በቅድሚያ ፍ/ቤቱ አንዱን መለየት ስላለበት ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሽን ያርማል፤ ወደፊትም ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በእስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

ከዚህ በላይ በተመለከተው የቅጣት ደረጃ መሰረት እርከኑን ለመወሰን እያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌን ለአራት እኩል በማካፈል የሚመጣው ስሌት በመንግስት የታወቁ ምልክቶች ላይ ለሚደረግ የመድፈር ወንጀሉ ከሦስት ወር እስከ አስራ አንድ ወር ቀላል እስራት ሲሆን ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ ከአስር ቀን እስከ ሰላሳ ቀን(ወይም አንድ ወር) ቀላል እስራት ነው። በዚህ መሰረት ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ መነሻ ቅጣቱ ሃያ(20) ቀን ሲሆን

በመንግስት ምልክቶች ላይ ለተፈፀመ የመድፈር ወንጀሉ ደግሞ ሰባት ወር ነው። ተከሳሽ ተደራራቢ ጥፋት ስለፈፀሙ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 184(1) (ለ) መሰረት የሁለቱ ቅጣት ድምር ሰባት ወር ከሃያ ቀን ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ 1 መሰረት በእርከን 5 ላይ የተመለከተ ስለሆነ የእርከን 5 ደግሞ ፍቅድ ስልጣኑ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1) መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ከላይ የተመለከተውን እርከን ከፍ አላደረገውም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ያላቀረቡ በመሆኑ የቅጣቱን እርከን ፍ/ቤቱ ዝቅ አላደረውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 5 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከስድስር ወር እስከ ዘጠኝ ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱም ተከሳሽን ሰባት ወር ቀላል እስራት፤ እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በአሁኑ ወቅት ሁለት የ 11 እና 6 ዓመት ልጆች አባት ስለሆኑ፤ ባለቤታቸውም የኤች አይቪ በሽተኛ ስለሆኑ (ማስረጃ የቀረበበት) እና የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ ተከሳሽ በመሆናቸውና ልጆች ደግሞ የቤተሰባቸው የቅርብ ክትትል እና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው በሕገ መንግስት አንቀፅ 36 ላይ የተደነገገ ስለሆነ፤ አገራቸውን ለረዥም ጊዜ በውትድርና ያገለገሉ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ለተከሳሽ አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የወደፊት ፀባይና አመላቸውን ማየቱ በቂ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ስላመነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ለብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት አንዲጠሩና ለመንግስት የዕህፊት ወጪም ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) አንዲከፍሉ ታዟል።

3 ኛ. የመተማመኛ ዋስትና ሲጠሩና የዕህፊት ወጪውን ሲከፍሉ ይለቀቁ።

4 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።